# ከናዝሬት/አዳማ አሳዛኝ ክስተት የምንማረዉ

አማኑኤል ዘሰላም
(work_amanuel@yahoo.com)

ነሐሴ 20 ቀን 2001

በቅርቡ የአንድነት ፓርቲ ናዝሬት/አዳማ ከተማ ያደረገው ስብሰባ «ይህ የኦሮሞ አገር ነዉ። በአማርኛ ስብሰባው መደረግ የለበትም» በሚሉና «የኦህድድ ካድሬዎች ናቸው» በተባሉ ጥቂት ግለሰቦች መረበሹን የሚገልጹ ዘገባዎችን በሰፊው ሳነብ፣ ከአሥራ ሰባት አመታት በፊት «ይህ የኦሮሞ አገር ነው። እዚህ መኖር አትችሉም» ተብሎ በበደኖ በአርባ ጉጉ የተገደሉ ኢትዮጵያዉያንን አስታወሰኝ።

የአንድነት ፓርቲ በናዝሬት/አዳማ ስብሰባ ስላደረገ ነገሩ ጎልቶ ወጣ እንጂ፣ ተመሳሳይ የሆኑ የብሄር ብሄረሰብ መብትን በመጠበቅና የኦሮምኛ ቋንቋን በማስፋፋት ስም፣ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብት ረገጣዎች ሲደረጉ ቆይተዋል። እየተደረጉም ነዉ።

ለምሳሌ ያህል በኦሮምያ አንድ ኢትዮጵያዊ ኦሮምኛ የማያውቅ ከሆነ ለማናቸውም አይነት የክልል መንግስት ሃላፊነት መወዳደር አለምቻሉን መጥቀሱ ይበቃል።

እርግጥ ነዉ ሙሉ ለሙሉ ኦሮምኛ ተናጋሪዎች ባሉበት ቦታ፣ ኦሮምኛ የማይናገር ሰው ተመራጭ ልሁን ቢል ያስቸግረዋል። ሕዝብ እንዲመርጠው ከሕህብ ጋር መግባባት አለበት። ቋንቋ ካልቻለ ደግሞ አጀንዳውን ለነዋሪዉ የሚያስተዋውቅበት መንገድ ከባድ ነው የሚሆንበት።

እንደ ናዝሬት/አዳም ፣ ደብረ ዘይት/ቢሾፍቱ፣ ድሬዳዋ፣ አሰላ ፣ ወሊሶ፣ ጂማ የመሳሰሉ አማርኛ ተናጋሪዎች በብዛት የሚኖሩባቸዉ፣ እጅግ በርካታ በሆኑ የኦሮሚያ ቦታዎች ግን ሁኔታዉ የተለየ ነው። በነዚህ አማርኛ ተናጋሪዎች በብዛት በሚኖሩበት ቦታዎች የተወለደ አንድ ኢትዮጵያዊ፣ ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት፣ ኦሮምኛ ካላወቀ ለክልል ምርጫ መቅረብ አይችልም። በአገሩ፣ በተወለደበት፣ አባቱ እናቱ አያቶቹ ቅድመ አያቶቹ በተቀበሩበት ቦታ፣ ኦሮምኛ ካለማወቁ የተነሳ፣ ከሌሎች ዜጎች ያነሰ መብት ይዞ እንደ «ዉጭ አገር ዜጋ» ሆኖ ነው የሚኖረው።

እንግዲህ በኢትዮጵያ ያለው አሳዛኝ እዉነታ ይህ ነው። ይህ አሳዛኝ እውነታና ችግር ቶሎ መፍትሄ ካልተገኘለት፣ ኦሮሚያ ነገ በዘር ላይ የተመሰረተ ደም መፋሰስ እንደሚጠብቃት መገመት አያስቸግረም። አንዳንድ አክራሪዎች «አማርኛ በግድ እንድንማር ተደርጎ ነው» ብለዉ እንደተነሱት ሁሉ፣ ነገ «ኦሮምኛን በግድ እየጫኑብን ነው» ብለው የሚነሱና ነፍጥ የሚይዙ ሊኖሩ እንደሚችሉ ማወቅ አለበን። ይህ ደግሞ ማለቂያ ወሌለው፣ በዘረኝነት ላይ ወደ ተመሰረተ ደም መፋሰስ ዉስጥ ነው የሚከተን እንጂ የሚያመጣልን አንዳች ጥቅም አይኖርም (ኢሕአዴግ ስልጣን እንደያዘ፣ ኦነግም የመንግስት አካል በነበረበት ወቅት ፣ በድሬደዋ ከተማ ኢሳዉና አማረኛ ተናጋሪዉ በአንድ ወገን፣ አክራሪ ኦሮምኛ ተናጋሪዎች ደግሞ በሌላ ወገን ሆነዉ ያስነሱትን ግጭት ማስታወሱ ይበቃል)

ታዲያ ምንድን ነው መፍትሄው ?

የዘረኝነትን ችግር በዘረኝነት የተለወሰ መድሃኒት በማቅረብ አይፈታም። የዘር ነገር ከተነሳ መጨረሻው አደጋ ነው። የሚያዋጣዉ ሁሉም ሰው ከዘሩና ከቋንቋም በላይ በማሰብ፣ በሰብዓዊነቱና በኢትዮጵያዊነቱ ተከባብሮ በእኩልነት እንዲኖር ማድረግ ሲቻል ብቻ ነው።

በዚህ አንጻር ይጠቅማሉ የምላቸዉን ሶስት ነጥቦችን እንደሚከተለው ለማስቀመጥ እሞክራለሁ።

## ቁቤ በግእዝ ተተክቶ ኦሮምኛን ከአማረኛ ጋር ብሄራዊ ቋንቋ ማድረግ

ቋንቋ መግባቢያ እንጂ የማንነት መግለጫ እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋል። ዜጎች በርካታ ቋንቋ ባወቁ ቁጥር የበለጠ ይጠቀማሉ እንጂ ማንነታቸዉን አያሳንሰዉም። በርካታ ቋንቋ ማወቅ ሰፊ የሥራ እድልን ይከፍታል። በኦሮምያ ያለ ወጣት፣ አማርኛ እንዲማር አለመደረጉ በአዲስ አበባ፣ በጎጃም፣ በጎንደር፣ በወሎ እንዲሁም በደቡብ ክልል የመሥራት የመኖር የመነገድ እድሉን ያጠብበታል። አማረኛ እንዲማር ቢደረግ ደግሞ ከኦሮሚያ ዉጭ ባሉ ግዛቶችም በነጻነት የመኖር እድል ያገጥመዉ ነበር። አማርኛ ፌዴራል ቋንቋ እንደመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዉያን ሊማሩት ይገባል ባይ ነኝ።

ኦሮምኛ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ህዝባችን የሚግባባበት ቋንቋ እንደመሆኑ፣ በኦሮሚያ ዉስጥ ብቻ ሳይሆን በመላዉ ኢትዮጵያ ሊያድግ የሚገባዉ ቋንቋ ነዉ። የላቲን ፊደል የሆነዉን ቁቤን በመተዉ በግእዝ ፊደል መጻፍ የሚቻልበት ሆኔታ ከተመቻቸ ኦሮምኛ ከአማረኛ ጋር ብሄራዊ ቋንቋ ተደርጎ ቢወሰድ፣ ኦሮምኛ የማያወቁ ወገኖቻችን ኦሮምኛን በፈቃደኝነት እንዲማሩ የሚያበረታታና ትልቅ ጥቅም ሊኖረዉ የሚችል ነገር ነዉ ብዬ አስባለሁ። (የመጀመሪያዉ የኦሮምኛ መጽሃፍ ቅዱስ የተጻፈዉ በግእዝ ፊደል ነዉ። መቼም በሚሲዮናዉያኖች የተወለደዉን ቁቤ የኦሮሞ ቅርስ ነዉ ብሎ መከራከር ያስቸግራል)

ሌላዉ የግእዝ ጥቅም ኦሮምኛ ተናጋሪዉንና አማረኛና ትግሪኛ ተናጋሪዉን ያስተሳስራል። ቢያንስ ቢያንስ የግእዙ ፊደል የሚያቀራረብና አንድ የሚያደርግ በእጃችን ያለ የኛዉ ቅርሳችን ነዉ።

## በዘር ላይ የተመሰረተዉን ፌዴራል አወቃቀር መቀየር

አሁን በሥልጣን ላይ ያለዉ አገዛዝ የዘረጋዉ፣ በዘርና በቋንቋ ላይ የተመሰረተዉ የፌዴራል አወቃቀር ነዉ፣ «የትግሬዎች ምድር የኦሮሞዎች ምድር፣ የአማራዎች ምድር» የሚለዉን ክፉ ነቀርሳ በምድራችን የተከለዉ። «ይህ የኦሮሞ ምድር ነዉ። በአማርኛ አትናገሩ» የሚለዉ አባባል የመጣዉም ኦሮሚያ የኦሮምኛ ተናጋሪዎች ብቻ እንደሆነች ተደርጎ በመታሰቡ ነዉ። ኦሮሚያ ከጅምሩ በኦነግና በኢሕአዴግ፣ ቋንቋን ብቻ መሰረት ባደረገ መልኩ የተመሰረተች ስለሆነች፣ በናዝሬት/አዳማ እንዳየነዉ ከኦሮምኛ ዉጭ ሌላ ቋንቋ አይኑር መባሉ ብዙም ሊያስደንቀን አይገባም።

ስለዚህ አንዱና ትልቁ መፍትሄ አሁን በኢትዮጵያ የተዘረጋዉን በቋንቋ ላይ ብቻ የተመሰረተዉን ፌዴራል አወቃቀር መቀየር ነዉ።

አንድ የትግሪኛ ተናጋሪ በነቀምቴ፣ በጅጅጋ፣ በደብረ ማርቆስ፣ ልክ በአዲግራትና በዉቅሮ ተምችቶት እንደሚኖረዉ ሁሉ መኖር የሚችልበት ሁኔታ መፈጠር አለበት።

ከጥቂት ወራት በፊት የአረና ትግራይ ሊቀመንበር አቶ ገብሩ አሥራት ድርጅታቸዉ በመቀሌ ሕዝባዊ ስብሰባ ባደረገ ጊዜ የተናገሩት አንድ አስደናቂ አባባል ነበር። «ኢትዮጵያዉያንን እስከሆንን ድርስ ትግራይ መሬታችን ነዉ። ኦሮሚያ መሬታችን ነዉ። ደቡብና ሶማሊያ መሬታችን ነዉ። አፋርም መሬታችን ነዉ። ለነርሱም ትግራይ መሬታቸዉ ነዉ። አማራም ትግራይ መሬቱ ነዉ። ሊኖርበት ይችላል። በዚህ ማመን አለብን።» ነበር ያሉት። ይህ አቶ ገብሩ ያሉት ተግባራዊ እንዲሆን ደግሞ ሁሉም ዜጎች ከየትኛዉም ዘር ይምጡ፣ በየትኛዉም ቦታ ይኑሩ፣ እኩል መብት ሲኖራቸዉና በዘር ላይ ባቻ የተመሰረተ ፌዴራሊዝም ሲቀየር ነዉ።

ፌደራሊዝሙ ቋንቋንና ዘርን ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚን፣ ጂኦግራፊን፣ የሕዝቡን ፍላጎት የመሳሰሉትን ባካተተ መልኩ ከተዋቀረ፣ የዘር ግጭትንና ዜጎች በአገራቸው ባይተዋር እንግዳ እንዲሆኑ፣ እንዲፈሩ የሚያደርገዉን ሁኔታ ማስወገድ ይቻላል።

## የግለሰብ መብት ከብሄር ብሄረሰብ መብት እንዲበልጥ በሕግ መደንገግ

በአገራችን አሁን ያለዉ ሕገ መንግስት፣ የግለሰብ መብት ያለገደብ መጠበቅ እንዳለበት ይደነግጋል። የዚያኑ ያህል ደግሞ የብሄር ብሄረሰብ መብቶች መከበር አለባቸዉ ይላል። ነገር ግን የግለሰበ መብት ከብሄር ብሄረሰብ መብት ጋር ሲጋጭ ለየትኛዉ ቅድሚያ እንደሚሰጥ በግልጽ አላስቀመጠም።

በአዳማ/ናዝሬት የተፈጠረዉ አሳዛኝ ክስተት፣ በብሄር መብትና በግለሰብ መብት መካከል ያለዉን ግጭት አጉልቶ ያሳየ ነዉ። ዜጎች በፈለጉት ቋንቋ መናገር፣ መሰብሰብ የግለሰብ መብታቸዉ ሲሆን የክልሉ መንግስት በመረጠዉ ቋንቋ ብቻ ስብሰባዎች እንዲደረጉ መወሰኑ ደግሞ የብሄር ብሄረሰብ መብት ነዉ።

በናዝሬት/አዳማ የሆነዉ ይሄ ነዉ። የናዝሬት/አዳማ ከተማ ነዋሪ አብዛኛዉ የአማርኛ ተናጋሪ ነዉ። ናዝሬት ኦሮሚያ ዉስጥ ስለተጠቃለለችና የኦሮሚያ ክልል መንግስትም (ኦሕዴድ) «ኦሮማኛና ኦሮምኛ ብቻ» ብሎ ስለወሰነ በከተማዋ ያሉ ዜጎች በአማርኛ የመማር፣ በአማርኛ ስብሰባ የማድረግ ወዘተረፈ መብታቸዉ ሙሉ ለሙሉ ተረግጧል። የብሄረ ብሄረሰብ መብት ከግለሰብ በላይ በመሆኑ።

የብሄር ብሄረሰብ መብቶች ከግለሰብ መብቶች ጋር በተጓዳኝ መከበር እንዳለባቸዉ ቢታወቅም፣ በሁለቱ መብቶች መካከል ግጭት ሲፈጠር ግን ቅድሚያ የሚሰጠዉ የቱ እንደሆነ በሕግ በግልጽ መደንገግ ይኖርበታል።

የግለሰብ መብት ከተጠበቀ የብሄር መብትም ይጠበቃል። የብሄር ብሄረሰብ መብት ተጠብቆ ግን የግለሰብ መብት ሊረገጥ ይቻላል። ስለዚህ የግለሰብ መብት ከሁሉ በላይ መሆን ይኖርበታል።

## መደምደሚያ

በቅርቡ በአገር ዉስጥ የሚንቀሳቀሱ በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች መድረክ በሚባለዉና፣ ገና ሕጋዊ ባልሆነዉ አካል ሥር በአንድነትና በጋራ መሥራት ስለሚቻልበት ሁኔታ እየተናጋገሩ ናቸዉ። እሰየዉ ብያለሁ።

ጂማ ታይምስ የተሰኘዉ ድህረ ገጽ እንደዘገበዉ፣ በቅርቡ የመድረክ የጋራ ማኒፌስቶ ይወጣል ተብሎ ይጠበቃል። በኦሮሞ ፌደራሊስት ንቅናቄ ፓርቲና በአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ መካከል በፌዴራል አወቃቀር አይነት ላይ ትልቅ ልዩነት እንዳለ ጅማ ታይምስ ዘግቧል።

የኦሮሞ ፌደራሊስት ንቅናቄ ፓርቲ በቅርቡ በናዝሬት/አዳማ ለተፈጠረዉ አሳዛኝ ክስተት ምክንያት የሆነዉን በዘር ላይ የተመሰረተዉን አሁን ያለዉን ፌደራል አወቃቀር ይደግፋል። የኦሮሞ ፌደራሊስት ፓርቲ ይህን በዘር ላይ የተመሰረተን አቋሙን እንዲመረምር በአክብሮት ጥሪዬን አቀርባለሁ።

ካልሆነም ግን ሌሎች የመድረኩ አባል ድርጅቶች የኦሮሞ ፌደራሊስት ፓርቲ የሚቀበለዉን በዘር ላይ የተመሰረተን የፌዴራል አወቃቀር ዉድቅ አድርገው ለመንቀሳቀስ መዘጋጀት አለባቸዉ። ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ፍቅር፣ አንድነት፣ እኩልነት፣ መከባበር እንጂ የዘር መከፋፈል አይደለም።